# ምርጫ ዛሬ ላይ ሆነን ነገን የምንወሰንበት ሂደት

ዳውድ ሁላን 10/01/12

በኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በየአምስት ዓመቱ የምክር ቤቱ አባላት ምርጫ ይካሄዳል፡፡ ይሁንና በተለያዩ ምክንያት አሁን ያሉት የጠቅላይ ምክር ቤቱ አባላት ከሁለት ተርም በላይ ያገለገሉ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ባለፈው አመት ማለትም በ2004 ዓ. ም ማገባደጃ ላይ ሊካሄድ ታስቦ የነበረው የምክር ቤት አባላት ምርጫ በጠቅላይ ሚኒስትራችን ሞት ምክንያት የተራዘመ በመሆኑ ዘንድሮ ማለትም ከመስከረም 27 ቀን 2005 ዓ. ም እስከ ጥቅምት 20 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ ባሉት ቀናት በሁሉም ብሔራዊ ክልሎችና በሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች በየደረጃው ባሉት መዋቅሮች ማለትም በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በዞን፣ በክልልና በመጨረሻም በሀገር አቀፍ ደረጃ ምርጫ እንደሚካሄድ ይታወቃል።

ስለ ምርጫ ሂደት ግልፅ የሆነ መረጃ ለህዝበ ሙስሊሙ ማድረስ ተገቢ በመሆኑ በየምርጫ ጣቢያው ወይም በየቀበሌው የግንዛቤ ማስጨቢጫ መድረክ በማዘጋጀት ህዝቡ ተገቢው ግንዛቤ እንዲኖረው መደረጉ ተገቢ ይመስለኛል። ሙስሊሙ ህብረተሰብ የምርጫ አስፈፃሚዎችንና የምርጫ ታዛቢዎችን በተገቢው ሁኔታ መምረጥ መቻሉ ለምርጫው መሳካት ቀዳሚው መመዘኛ ነው።

አንዳንድ ግለሰቦች ሆን ብለው የኢትዮጵያን ዑላማዎች የፈትዊና የደዕዋ ምክር ቤት የሚያስተላልፈውን ውሳኔዎች በሙስሊሙ ህብረተሰብ ተቀባይነት እንዳይኖረው ለማድረግ ሲሯሯጡ ይታያሉ። ለአብነት ያህል ለመጥቀስ የምንመርጠው የሃይማኖት መሪዎቻችንን እንጂ የፖለቲካ መሪዎቻችንን ባለመሆኑ ምርጫው መካሄድ ያለበት በቀበሌ ሳይሆን በእምነት ቦታችን በመስጂድ፣ የታሰሩት ሰዎች ካልተፈቱ በምርጫ አንሳተፍም ወዘተ´ የሚሉ ውሃ የማይቋጥሩ ምክንያቶችን በመደርደር ህዝበ ሙስሊሙ በምርጫው እንዳይሳተፍ ለማድረግ ከታች ላይ ሲዋትቱ ይታያሉ።

እኛ በቀበሌ ደረጃ የመረጥናቸው ተወካዮቻችን በወረዳ ደረጃ ይገናኙና ለዞን ተወካይ ይሰይማሉ እነዚህ ለዞን ደረጃ የተወከሉ ደግሞ ይሰባሰቡና የክልል ተወካየ ከሰየሙ ቡኋላ በመጨረሻም የየክልሉ ተወካዮች በአገረ አቀፍ ደረጃ በመሰባሰብ የኢትዮጵያ ሙስሊም ማህበረሰብን የሚመራ አካል በአገር አቀፍ ደረጃ ይሰይማሉ ማለት ነው። ከዚህ ሂደት ማየት የሚቻለው የትኛውም አካል ጫና ሊያሳድር የሚችልበት አሰራር ሊኖር አይችልም።

እንግዲህ ከዚህ የውክልና ሰንሰላት በግልፅ ማየት የሚቻለው በአገር አቀፍ ደረጃ የሚመረጡት የእምነታችን መሪዎች እኛ በቀበሌ ደረጃ የመረጥናቸው መሆኑን መገንዘብ ይገባል። ስለዚህ ሙስሊሙ ማህበረሰብ እጩዎቻችንን ከማቅረብ ጀምሮ ድምፃችንን ለማን መስጠት እንዳለብን ለይተን ማወቅ፣ ለነገ የሃይማኖት መሪዎቻችን ጥንካሬ ወሳኝነት ትልቅ ድርሻ እንዳለው ሊታወቅ ይገባል።

አንዳንድ ሰዎች ምርጫው የመንግስት መዋቅሮችን ማለትም  ከቀበሌ ጀምሮ ያለውን መጠቀምን በመልካም አይመለከቱትም፡፡ እነዚህ ሰዎች ያለ በቂ ምክንያት ምርጫው በቀበሌ መካሄድ የለበትም እያሉ በመቀስቀሳቸው ምክንያት አንዳንድ የሙስሊሞችን ወደ ተሳሳተ ድምዳሜ እንዲደርሱ አድርገዋል።

አሁን የሚካሄደውን የእስልምና ምክር ቤት ምርጫን በተመለከተ ገሚሱ ምርጫው መካሄድ ያለበት የመንግስት መዋቅር በሆነው ቀበሌ መሆንአለበት  ሲሉ  ሌሎች ደግሞ ከቀበሌ ውጭ በሆኑ የእምነት ቦታዎች ማለትም በመስጂድ መሆን አለበት ሲሉ ይደመጣሉ። ለመሆኑ ምርጫው ከዚህ በፊት ሲካሄድበት በነበረው ቀበሌ መሆኑ ያለውን ፋይዳና ጉዳት ተንትኖ በማሳየት ማስረዳት የሚቻል ይመስለኛል።

በቅድሚያ ምርጫው በቀበሌ መካሄዱ ጠቀሜታው ሁሉን አቀፍና ወጥነት ያልው እንዲሆን ያደርገዋል ብዬ አስባለሁ። ይህም ሲባል በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል (በአርብቶ አደሩም ሆነ በአርሶ አደሩ) የቀበሌ መዋቅር የሌለበት አካባቢ ባለመኖሩ መራጮቹ ያለምንም ችግር በአካባቢው ምርጫ ሊያካሂድ ይችላል። በመሆኑም ሁሉን አቀፍና  ወጥነት ያለው  ምርጫ ማካሄድ ይቻላል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ሁለተኛው ምርጫው በመስጂድ የሚካሄድ ከሆነ በከተሞች በተለይ እንደአዲስ አበባ ባሉ ትላልቅ ከተሞች በአንድ ቀበሌ ውስጥ ሁለትና ከዚህ በላይ መስጂዶች ያሉበት ሁኔታ ስለሚኖር ህዝበ ሙስሊሙ በየትኛው መስጂድ መምረጥ እንዳለበት ሊያውቅ አይቻልም፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ የድምፅ አሰጣጥ ስርዓቱ ላይ የታአማኝነት ጥያቄ እንዲነሳ በር ከፋች ይሆናል፡፡ ምክንያቱም አንድ ግለሠብ በየትኛው አጥቢያ መስጂድ ተመዝግቦ ድምፅ ይሰጣል የሚለው ጉዳየ ሌላው አጨቃጫቂ ጉዳይ ይሆናል?

ሶስተኛው ከፀጥታ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን መመልከት ይቻላል፡፡ መስጂዶች ቤተ አምልኮ በመሆናቸው የፀጥታ ሃይሎችን በእነዚህ ቤተ እምነቶች መመደብ አግባብነት ያለው ሊሆን አይችልም፡፡ መንግስት ህዝብ በሚሰበሰብበት ቦታ ሁሉ የፀጥታ ስራ የመስራት ግዴታ እንዳለበት ይታወቃል፡፡ ሆኖም ግን በቤተ እምነቶች ውስጥ የሚደረግ የፀጥታ ስራ  የእምነት ስረዓትን ይጋፋል በሚል ከሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ሲተች ይሰማል።

የፀጥታ ጥበቃ ስራ የመንግስት አንዱ ሃላፊነት እንዲሁም የዜጎችም መብት እንደሆነ መታወቅ ይኖርበታል። የፀጥታ ጥበቃ የሚደረገው አሁን ምርጫ ስለሚካሄድ ሳይሆን ከዚህን በፊት በነበረው ልምድ ህዝብ በብዛት ይሰበሰብባቸዋል ወይም ይገኝባቸዋል በሚባሉ ሁነቶች፤ ለምሳሌ፣ በአዳራሽም ሆነ ከአዳራሽ ውጭ በሚደረጉ ስብሰባዎች፣ የድጋፍም ሆነ የተቃውሞ ሰልፎች፣ የእምነት  ስርዓት በሚፈፀምባቸው ቦታዎች (በጥምቀት፣ በመስቀል፣ በኢድ፣ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ከአደራሽ ውጪ የአምልኮ ስርዓት ሲኖራቸው፣ የኢሬቻ በአል  ወዘተ)  ብቻ ቁጥሩ በርከት ያለ ህዝብ በሚሰበሰብበት ጊዜና ቦታ ሁሉ  መንግስት የፀጥታ ጥበቃ የማድረግ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

ከላይ ለመጠቆም እንደተሞከረው ይህ ምርጫ የአምልኮ ስፍራ በሆነው መስጂድ የሚካሄድ ከሆነ መንግስት የሚመድባቸው የፀጥታ ሃይሎች በተገቢው ሁኔታ ስራቸውን ለመወጣት አይችሉም፡፡ ስራቸውን በአግባብ

እንወጣለን ቢሉ ደግሞ የእምነቱ ስርዓት ምን ያህል እንደሚጣስ እነዚህ ምርጫ በመስጂድ መሆን አለበት የሚሉ ሰዎች የተገነዘቡት አይመስለኝም፡፡

በህግ ቁጥጥር ስር ያሉ ግለሰቦችን በተመለከተ በአገራችን የህግ የበላይነት ይንገስ የሚል አቋም የሚኖረን ከሆነ በህግ የተያዘ ጉዳይን ከምርጫ ጋር ማያያዝ ተገቢ መስሎ አይታየኝም። እነዚህ ሰዎች በህግ አግባብ በመዳኘት ነፃነታቸውን አሊያም ጥፋተኛነታቸው መረጋገጥ ሲገባ ከህግ መስመር ውጭ ዳኝነት መፈለግ ተገቢ አይመስለኝም።

የህግ የበላይነት በደጋፊ ወይም በቲፎዞ ሊሸረሸር እንደማይገባ ሁላችንም ከስምምነት ላይ ሊያደርሰን የሚገባ ነገር ይመስለኛል። የአንዲት አገር ሉአላዊነትና የዜጎች እኩልነት የሚረጋገጠው የህግ የበላይነት ሲተገበር መሆኑ መታወቅ አለበት። ይህ ካልሆነ የአገራችን ህግ አንካሳ እንዲሆንና ደጋፊ ወይም ቲፎዞ ያለው ከህግ በላይ ሌላው ደግሞ በተቃራኒው እንዲሆን የሚያደርጉ አሰራሮችን ወደ መተግበር ልንመለስ ነው።

አብዛኛው ሙስሊም ትክክለኛውን የእምነቱን ስርዓት የሚፈፅሙና የእምነት መሪዎቻችንን ለመምረጥ እንደተዘጋጀን ሁሉ ጥቂቶች ደግሞ ጥቅም ያስገኝልኛል የሚሉትን ድብቅ አጀንዳቸውን ለመተግበር ደፋ ቀና የሚሉበት ወቅት መሆኑን መታሰብ ይኖርበታል፡፡ ፀጥታ መደፍረስ ለአብዛኛዎቻችን ጉዳት ያስከትላል ብለን ብናምንም ለአንዳንዶቻችን ደግሞ እንደ መና የሚናፈቅ እንደሆነ ካለፈው ልምዳችን መገመት ብዙ የሚከብድ አይመስለኝም።

አንዳንድ ግለሠቦች ምርጫው በቀበሌ የሚካሄድ ከሆነ መንግስት የሚፈልጋቸውን ሰዎች ሊያስመርጥ ይችላል የሚል ስጋት ይታይባቸዋል፡፡ እንደ እኔ ይህ ስጋት ሊሆን አይገባም፡፡ ምክንያቱም ህገ መንግስቱ የመጀመሪያው ገዥ ሰነድ ነው፡፡ ሃይማኖትና መንግስት በግልፅ ድንጋጌ መለያየታቸው ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም ምርጫው በቀበሌም ተካሄደ በመስጂድ መንግስት የሙስሊሙን አመራር ሊወስን የሚችልበት መንገድ ከቶ ሊኖረው አይቻለውም፡፡ መንግስት ጣልቃ መግባት የሚፈልግ ከሆነ ምርጫው የትም ቢካሄድ ልናስጥለው የምንችልበት ሁኔታ ይኖራል ብዬ አላስብም። ነገር ግን መንግስት የሙስሊሙን አመራር ምርጫ ላይ ተፅእኖ በመፍጠር ሊያገኘው የሚችለው የፖለቲካ ትርፍ እንደሌለ ማንም ቅን ልቦና ያለው ሰው ሊረዳው የሚችለው እውነታ ነው፡፡

እንደ እኔ እኛ መስሊሞች የምንመርጣቸው የሃይማኖት መሪዎቻችን የሃይማኖቱን መርህ ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ እስላማዊ አንድነታችንን የበለጠ የሚያጠናክሩና የሚያስፈፅሙ እንዲሁም ከሌሎች የእምነት ተከታይ ወንድሞቻችን ጋር ተቻችለን የምንኖርበትን ሁኔታ የሚሰብኩ፣ የአገረችንን ሰላምና ልማት የበለጠ ጠንካራና ዘለቄታዊነት እንዲኖረው የሚያደርጉ መሆን መቻል አለባቸው።

ሙስሊሙ ህብረተሰብ በነፃነት የሚመርጣቸው የሃይማኖት መሪዎች የአገራችንን ህገ መንግስት መሰረት አድርገው ህዝበ ሙስሊሙን የሚያስተባብሩና የሚመሩ በመሆናቸው መንግስት ጣልቃ በመግባት እከሌን ምርጡ እከሌን አትምረጡ የሚልበት ሁኔታ ይኖራል ብዬ አላስብም።

የዚህ ምርጫ ዋነኛ ዓላማ ነፃ ቀጥተኛና ግልፅ በሆነ መንገድ ሙስሊሙን ማህበረሰብ ለሚቀጥሉት አምስት አመታት የሚመሩትን ተወካዮች መምረጥ መቻል ነው፡፡ እነዚህ የሙስሊሙ ማህበረሰብ የሃይማኖት መሪዎች በቀዳሚነት እኛ የእምነቱን ተከታዮችን ማገልገል ቢሆንም፣ በአገራችን ኢትዮጵያ ላይም ከፍተኛ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅእኖ ሊፈጥሩ እንደሚችሉ በማወቅ ሁላችንም በንቃት በምርጫው ላየ ልንሳተፍ ይገባል።

ስለዚህ ሙስሊሙ ማህበረሰብ በነቂስ ወጥቶ በሃቅ የቆሙ፣ ሃላፊነታቸውን ለመወጣት ብቃት ያላቸው፣ የሃይማኖቱን መርህ ጠንቅቀው የሚያውቁና ለሃይማኖታቸው ተገዢ የሆኑ፣ በመልካም ስነ-ምግባራቸው በህብረተሰቡ የተመሰከረላቸውን፣ በአርአያነታቸው የሚታወቁ ለሙስሊሙ አንድነት በፅናት የሚቆሙ አመራሮችን በመምረጥ የአገራችንን ሰላምና ልማት ማስቀጠል ይኖርብናል፡፡ ከዚህ ቀደም አንዳንድ አክራሪ ሃይሎች የተሳሳተ መረጃዎችን በህዝበ በማስረፅ ቀላል የማይባል የህብረተሰብ ክፍልን ወደ ተሳሳተ ድምዳሜ እንዲሄድ አድርገዋል። ዳግም እንደዚያ ያለ ስህተት ልንሰራ አይገባንም።

እነዚህ የግል ጥቅማቸውን የሚያሳድዱ አንዳንድ ግለሰቦች ሙስሊሙ በምርጫው እንዳይሳተፍ ቀላል የማይበል ፕሮፓጋንዳ እያሰራጩ ይገኛሉ። ሆኖም የእነዚህን ሰዎች አካሄድ ቆም ብሎ መመልከት ተገቢ ይመስለኛል። እያንዳንዳችን ዛሬ የምንሰጠው ድምፅ የነገን የሃይማኖት መሪዎቻችን ብቃት ላይ ወሳኝነት ይኖረዋል። በምርጫ ሂደት አንድ ድምፅ ልዩነት እንደምታመጣ ከግንዛቤ በማስገባት ሁላችንም ድምፃችንን ለማነ መስጠት እንዳለብን በደንብ ልናጤነው ይገባል።

አሁን በሚካሄደው ምርጫ ላይ ተሳታፊ ለመሆን ሙስሊሙ ህብረተሰብ በቅድሚያ ድምፅ የሚሰጥበት የቀበሌ ነዋሪ መሆንና የቀበሌ መተዋወቂያ ሊኖረው ይበባል። የቀበሌ መተዋወቂያ ለምርጫ ተሳታፊነት አስፈላጊ የሚሆንበት ዋንኛ ምክንያት ከሌላ ቦታ ማለትም ያለቀበሌያቸው ሊመጡ የሚችሉ ሌሎች ሰዎችን በቀላሉ ለመለየት ከማስቻሉም በላይ ለፀጥታ ቁጥጥርም አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል።

ከዚህ በተጨማሪ ማንም በመራጭነት የሚሳተፍ ግልሰብ ወንድም ሆነ ሴት ዕድሜው ከ18 አመት በላይ መሆን ሲኖርበት፣ በተመራጭ እጩነት ለመቅረብ ደግሞ አንስተኛው የእድሜ ገደብ ሰላሳ መሆን መቻልና እንዲሁም እጩዎች ወንዶች ብቻ እንደሚሆኑ የሃይማኖቱ መርህ ይደነግጋል።

የምርጫን ታማኝነትና ግልፅነት ከሚያሳዩ ጉዳዮች መካከል ቀዳሚው የምርጫ አስፈፃሚዎች ወይም አስመራጭ አካሎች እንደሆኑ ይታወቃሉ። ስለዚህም ሙስሊሙ ህብረተሰብ የምርጫ አስፈፃሚዎችን በጥንቃቄ እንደመረጥን ሁሉ ድምፃችንንም የምንሰጠውን እጩ ጠንቅቀን ማወቅ ይኖርብናል።

አንዳንድ ስግብግብ ግለሰቦች የግል ጥቅማቸው አማሎአቸው ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ የህዝብንና የአገርን ጥቅም አሳልፎ ከመስጠት ወደ ኋላ እንደማይሉ ከቅርብ ጊዜ ድርጊቶች ማየት ይቻላል። እነዚህ በጊዜያዊ ጥቅምን የናወዙ፣ አገራችንንና የአፍሪካ ቀንድን ነባራዊ ሁኔታ ያልተገነዘቡ፣ ድርጊታቸው ምን ያህል በእሳት መጫወት እንደሆነ የተገነዘቡት አይመስልም። የተፈናጠጡት የአክራሪነት ፈረስ ያልተገራ፣

ልጓም የሌላው መነሻው እንጂ መድረሻው የማይታውቅ፤ ለሁላችንም የማይበጅ ነገርን የሚያመጣ መሆኑን ባለመገንዘባቸው የማይገባ ድርጊት ላይ ተሰማርተው ይታያሉ።

እንደ ኢትዮጵያ ባለች ዘርፈ ብዙ ልዩነቶች በሚስተዋሉበት፣  የኀረቤቶቻችን ያለመረጋጋት ታክሎበት እስካሁን በአገራችን ኢትዮጵያ በሃይማኖት ረገድ ግጭት ተከስቶ የማያውቅበት ዋነኛ ምክንያት  የሁሉም የሃይማኖት አባቶች ተከታዮቻቸውን  ስለመቻቻልና አብሮነት  መስበክ በመቻላቸው እንደሆነ  ሁላችንም የምንገነዘበው እውነታ ነው።

ይህንን የቆየ የመቻቻል ባህላችንን በሚሸረሽር መልኩ የሚንቀሳቀሱ አንዳንድ የሃይማኖት ተከታዮች የሚያደርጉትን ከመረን የወጣ ድርጊት በዝምታ ልንመለከተው አይገባም። |"ሳይቃጠል በቅጠል"´ ይላሉ አበው ሲተርቱ። መንግስት ማለት ህዝብ ማለት ነው። መንግስት የእኛ ተወካይ ነው፤ በመሆኑም የህግ የበላይነት ሊረጋገጥ የሚችለው የሁላችንም ተሳትፎ ሲታከልበት ነው። ስለዚህ እያንዳንዳችን ህግን ማክበር ብቻ ሳይሆን ማስከበርም ግዴታችን መሆኑን አውቀን፣ ከህግ አግባብ ውጪ የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦችን ከመንግስት ጎን በመሰለፍ  ወደ ህግ ልናመጣቸው ይገባል እላለሁ።

አንድ የዴሞክራሲ መርህ እንዲህ ይላል  “ማንም እጁን መዘርጋት የሚቻለው ሌላውን እስካልነካ ድረስ ብቻ ነው” የትኛውም የሃይማኖት መሪም ሆነ ተከታይ  ሃይማኖቱን ማራመድ የሚቻለው የሌላኛውን መብት እስካከበረ ድረስ መሆኑን መገነዘብ የሚያስቸግር አይመስለኝም። በአንዳንድ  ሃይማኖትን እንደሽፋን በማድረግ የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦች እየተከተሉ ያሉት  ነገሮች  እንኳንስ ለህዝብና ለአገር ለራሳቸውም እንደማይበጅ ያወቁት አይመስለኝም። ወልደን የምንስምበትና ሰርተን የምንከብርበት አገር ሰላም ስትሆን ነው። በአገር ሰላም ላይ የሚደረግ ድርድር መቼም ይኖራል ብዬ አላስብም።